# ልቦለድ

## የሚስጥረ ማመልከቻዎች

ከጌቱ ሀይሉ

መድሃኔ አለም ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ካለው ቤንዚን ማደያ ጋ ቆማ ታክሲ ትጠብቃለች። ሚስጥረ ትባላለች። ከቤንዚን ማደያው ጋር ተያይዛ ካለችው አነስተኛ ቡና ቤት የሚወጡና የሚገቡ ደምበኞችዋ (አብዛኞቹ መምህራን) አይኖች ሳያርፉባት አያልፉም። እሷም ብትሆን ማስተዋሏ አልቀረም። ሚስጥረ እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች "በአይንዋ ቂጥ" (በስዋ አባባል) ነው የምትገረምማቸው።

ከወደ አስኮ መስመር የሚመጡ ታክሲዎችን ትቃኛለች። አጠገቧ ሊደርሱ ትንሽ ሲቀራቸው የቀኝ አጅዋን ሌባ ጣት ትቀስራለች። ሹፌሩ በተቀመጠበት መስኮት ትይዩ ታነነብስና (ፒያሳ) ትላለች። ወደ ግራ ስትዞር በጆሮዎቿ ትክክል የሚቀረው የተፈጥሮ ጸጉርዋ ላይ የቀጠለችው ሰው ሰራሽ ጸጉር ጉንጉኖች በህብረት ወደ ቀኝ ይዘማሉ። ወደ ቀኝ ስትዞር ደግሞ ወደ ግራ። ምናልባት ልጭንቅላቷ ላለመታዘዝ ይሆን? ብቻ ባንድነት መዝመማቸውና ቀጥ ማለታቸው ከጥቁር ቀጫጭን ሽቦዎች የተሰሩ ያስመስላቸዋል።

ሁለት ታክሲዎች ሞልተው፤ ሶስተኛዋን ውይይት ጀርባ መቀመጥ ባለመፈለግዋ አሳልፋ፤ በአራተኛዋ ጉዞ ጀመረች። ባካል ወደ ፒያሳ በሃሳብ ወደ ኋላ። ስራ ለመቀጠር "ማመልከቻ" ያስገባችባቸውን መስሪያ በቶችና ሁኒ<_tawoc mastawes jemerec::

"አይ ነቢያት! እሱን በሎ ደግሞ ነቢይ! ነቢያት ብሎ ደግሞ ለሱ ስም! ስሙን ቄስ ይጥራውና! እንደዛሬው በቅዳሚ_ ቀን ነው አይደል ያኔ እነሱ መስሪያ ቤት ስመላለስ! 'ግድ የለሽም አስቀጥርሻለሁ' ብሎኝ የወጣሁለት! እማዬ ትሙት እንደሱ የተጫወተብኝ የለም! አይ ምላስ!መቸም ያውቅበታል። አኔማ በቃ አሱ ሲያወራልኝ፤ በቃ የእውነት የተቀጠርኩ መስሎ ይሰማኝ ነበር። ምንዋ ሞኝ ነበርኩ ግን!

'ፈተና አዘጋጅ ኮሚቴው ውስጥ ስላለሁበት ምንም አትስጊ። በኔ ጣይው...' ቅብጥርሶ ሲለኝ እንዴት አላምነው!? ማንም ቢሆን እንዲህ ቢባል ያምናል። በሱ አነጋገር፣ በዚያ ላይ አለባበሱ! በቃ ልክ ባለስልጣን ነው እኮ የሚመስለው። አኔ ቢያንስ ቢያንስ ያንድ ክፍል ሃላፊ ይሆናል ብዬ ነበር የገመትኩት። እረ አሱማ ጉራው ስራ አስኪያጅ ያስመስለዋል!

አሁን አሱን ትቶ ያን ኩሩሩ ድውይ ሰውዬ ማን ማኔጀር ነው ብሎ ይገምታል!? አሁን በየነ ከዚያ ጉድ ባያወጣኝ ኖሮ ምን ይውጠኝ ነበር! አይ በዩ 'እንጋባ' አያለባይጨቀጭቀ አሱው ይሻላል። አግዜር ይስጠው አሱ ባይኖረኝ ኖሮ ይኸኔ ዲቃላዬን ታቅፌ ቁጭ ብዬ እቀር ነበር። አይ በዩ ጨባው!

'ግዋደኛዬ ታማለችና ያን ሆስፒታል የሚሰራውን ግዋደኛህንአስችግርልኝ'ስለው፤'የትዋ?'አንክዋን አላለም። ግዋደኛውስራሱ ቢሆን ጥሩ ሰው ነው። 'ያንድ ቀን ስህተት ነው፤ ለበዩ አትንገርብኝ፤ ችግሩ የራሴ_ ነው።'ስለው 'እሺ' ማለቱ። ግን ለበየነ ነግሮት ይሆን? አልነገረውም። ነግሮትማ ቢሆን ኖሮ!

ግን ነግሮት ቢሆንስ ኖሮ፤ ምን እንዳያደርገኝ! አይፈልጠኝ፤ አይቆርጠኝ!ግፋ ቢል መለያየት ነው! ላልጠፋ ወንድ! ግን አሱው ሳይሻለኝ አይቀርም። ምንም ቢሆን በወር ድሞዝ በተቀበለ ቁጥር የሚገዛልኝ ሽቶ፣ትያትር፣ሲኒማ መጋበዙ ራሱ፤ስንት ነገር አለ!

አንዳንዶቹማ ደረቆች! ጠብም አይላቸው! በዩ ግን የምጠላበት ጸባዩ 'አት ሊስት' በሳምንት አንዴ አንኳን 'ናዪት ክለብ' እንግባ ብሎኝም አያውቅም። 'ፓርቲ እንሂድ'ስለው ከስንት አንድ ቀን ነው የሚስማማው።'ዛሬ ፕሮግራሜ ....'የሚል ፈሊጥ አለው።"

እሱን ደስ የሚለው በየወሩ ገንዘቡን እየከሰከሰ መደርደሪያ ሙሉከ ገጠገጠው መጽሃፍት አንዱን አንስቶ፤'ሚስጥር ይህቺን አንብቢያት፤ ባለፈው ሰሞን የወጣች ቆንጆ መጽሀፍ ናት።'ማለት ነው። እኔ ለራሴ አንደማንበብ የሚያስጠላኝ የለም። ሳነብ አንቅልፌ ይመጣብኛል።"

'እንቁላል ፋብሪካ' አየተባለ የሚጠራው አካባቢ ደርሰው፤'ወራጅ ፣ ወራጅ አለ!'ብሎ አንዱ ተሳፋሪ ለመውረድ ታክሲዋ ስታቆም ነበር ከሃሳብዋ የነቃችው። ወዲያውታክሲዋ በርዋን ዘግታ ጉዞ ከመጀመርዋ ወደ ትውስታዋ ተመለሰች። ጎረምሳው የታክሲ ሹፌር ጉሮሮውን አየጠራረገ ንግግር ለመክፈት ቢሞክርም አልሰማችውም።

"ትሩፋት፤ ትሩፌ ነች ነብያት መዝገብ ቤት አንደሚሰራ የነገረችኝ። ጎበዝ ናት።ፈተናውን አልፋ የተቀጠረችው እሷው ናት። ምነው የሷን ጭንቅላት ቢሰጠኝ! ነቢያት ሺፈራው የመዝገብ ቤት ጸሀፊ። ድንቄም የፈተና አዘጋጅ ኮሚቴ አባል! ከነቢያትስ ደመቀ ይሻላል። እውነቴን ነው፤ ገገማ ቢሆንም ቁርጡን የሚናገረው ይሻላል። አንደ ነቢያት ቀልጣፋ ቢሆንማ ኖር ይሄኔ_ ስንትዋን ያወጣ ነበር! ገና አንድ ሁለት ቃላት ከመለዋወጣችን፤ 'የኔ እህት ልረዳሽ የምችል አይመስለኝም። መስሪያ ቤታችንም ቢሆን በዘመድ አዝማድ የሚሰራበት አይነት አይደለም። ሊ_ላው ቢቀር በኔ በኩል የማይሆን ነገር ነው። ቦታው መመዘኛውን ለሚመጥን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ክፍት ነው። ፈተና እንሰጣለን፤ አናወዳድራለን ማለት ነው። የውድድሩ አሸናፊ ይቀጠራል። በዚህ መሰረት ነው ያንቺንም ጉዳይ የምመለከተው።'አለኝ። ገገማ ነው።አኔ ነኝ ያስተካከልኩለት፤ እሱማ አንደዚህ መናገርም አይችልበትም።' ................ 'በሳቅ ጦሽ ልል ምንም አልቀረኝ! መቼስ ምን ላድርግ ለቅጥር አመልካች አይደለሁ፤ አንደምንም ቻልኩት። በኋላ በዩ ነገረኝ ስድስት ኪሎ ማኔጅመንት ግራጁæየት ነው ብሎ። ከበየነ ጋር አንድ ሁለት ቀን አይቶኝ አይደል '...ሜሲሪያ ቤታቺኒ ...'ያለው። በትውውቅ አንደማይጠቅመኝ ማስጠንቀቁ ነው በሱ ቤት። ራሱ በየነስ ራሱ በየነስ ቢሆን 'ለምንልኝ'ብለው 'እምቢ' አይደል ያለው! 'ፕሪንሲፕል'የሚሉት ነገር አላቸው። አይ ደመቀ! የኛ ሃቀኛ!'ኮከብ ሰራተኛ'ተብሎ ይሸለማታ!ግን ቢሆንም እስው ቁርጤን የነገረኝ ይሻለኛል። ያኔማ ለፈተናም አልሄድኩ፤ ላላፍ ነገር።

ራስ ደስታ ሆስፒታል አካባቢ ሲደርሱ የታክሲው ሹፌር ሌላ የካሴት ክር አስገባ።ሚስጥረን 'ካረቢያን ኪዊን' የሚለው ሙዚቃ ወደ ለላ ትውስታ ቀየራት። የሹፌሩአይኖች አጭሩ ጅንስ ቀሚስ በከፊል ያጋለጣቸው፤ ከጉለበቶችዋ በላይ እስክ ቀሚሱ ጠርዝ ድረስ ያለው የሰውነት ክፍልዋ ላይ አርፈዋል።አላስተዋለቻቻቸውም።

"አይ ዳኒ! ይሄኔ አንተ አሜሪካን ሀገር ተንደላቀህ ትኖራለህ። እኔ እዚህ በዚህ ሙዚቃ ሁሌ አስታውስሃለሁ።'ካረቢያን ኪዊን'የሚለውን ቀይረህ 'ኢትዮጵያን ኪዊን'እያልክ ስትዘፍንልኝ የነበረው አይረሳኝም። የሸኘትህ ቀን ዋዜማ ፌርዌል ላይ ስንት ጊዜ እንደደነስንበት፤ ያልከኝ ሁሉ አይረሳኝም።ይሄኔ አንተ እንክዋን ዘፈኑን እኔንም ረስተህኝ የሆናል። አይ ዳኒ! 'ዳኒ ቦይ በይኝ ስትጠሪኝ' ያልከኝ ትዝ የልሃል?እዚያ መቼም 'ዳኒ ቦይ' እያሉ ነው የሚጠሩህ። 'ሄሎው ዳኒ ቦይ! ሃው ዱ ዩ ዱ!' እንዴት ደስ ይላል!ታድለህ!እኔም አንድ ቀን ከዚች ሃገር መውጣቴ አይቀር! ዳኒ ቃሉን ካላጠፈ ወደ አሜሪካ እወስድሻለሁ ብሎኝ ነበር። ቢሆን ነው እንጂ ታድያ እስከ ዛሬ ፖስት ካርድ እንኳን ሰው አይልክም?!

ቢሳካልኝማ ስራ፣ ምናምን ከማለት መውጣቱ ነበር የሚሻለኝ።"

'ካረቢያን ኪዊን' አብቅቶ ወደ ሌላ ትውስታ፤ ወደ ዋናው መለሳት። ግራ እግርዋ ላይ የጫነችውን የቀኝ እግርዋን አውርዳ ግራ እግርዋን የቀኝ እግርዋ ላይ ጫነችው። የታክሲ ሹፌሩ አይኖች አረፉባቸው። አላስተዋለቻቸውም።

"ከሁሉም የተጫወተብኝ ግን ደጀኔ ነው። እሱ እንደሸወደኝ ማንም አልሸወደኝም። እንደ ነበያት ስልጣን አጥቶ አይደለም። የሰራተኛ ክፍል ሃላፊ ነው አሉ። ማስቀጠር ቢፈልግ በደንብ ይችል ነበር። መጀመርያ ጥሩ ሰው መስሎ ኋላ ማለት አመጣ እንጂæ^። 'አይዞሽ ሚስጥረ ሁሉንም ነገር በኔ ጣይው፤ኦኬ!'ከዚያ እጆቹን ጠረጴዛ ላይ ደግኖ፤ ጣቶቹን እያፍተለተለ፤ ቅንደቦቹን ሸብሸቦ፤ ከናፍሩን ወደፊት እየለጠጣቸው፤ 'ግን ሚስጥረ እንደምታውቂው አንድ ሰው ላንድ ሰው አንድን ጉዳይ ሲፈጽምለት በሌላ ጊዜ ያ ሰው፤ ማለቴ ጉዳዩ የተፈጸመለት ሰው በተራው ያን የፈጸመለትን የሚረዳበት ሁኔታ፣ መንገድ ካገኘ ወደ ኋላ እንደማይል የምታውቂ የመስለኛል። እና ተግባባን?....'እኔ ልድት እንኳን ይህችንና የዝንብ ምንትስ እናውቃለን አልኩና በልቤ፤ ባፌ 'እሺ!'ነዋ! መጀመሪያ እኔ የሱ ጉዳይ ፈጻሚ ሆንኩ። እሱ እኔ እርዳታ በምፈልግበት ጊዜ ወደ ኋላ እንደማይል ሙሉ በሙ=ሉ በመተማመን። አይ ደጀኔ! መጨረሻ ላይ ምናለኝ ታድያ?!'ሚስጥረ ምንም ማድረግ አልችልም። ፍቅር ሌላ፤ ስራ ማስቀጠር ሌላ።'አይን አውጣ ደረቅ!እሱን ብሎ ሃቀኛ!ስንትዋን እንዲህ ብልዋት ይሆን? ታድያ ከሱ ደመቀ አይሻልም?"

ታክሲዋ የማዘጋጃ በት ዋናው በራፍ ጋ ልትደርስ ትንሽ ሲቀራት ቆመችና ተሳፋሪዎችዋን ማራገፍ ጀመረች። ምንም እንኳን ከስልሳ ሳንቲም በላይ የሚሆኑ ዝርዝር ፍራንኮች ቢኖርዋትም ሰሞኑን የምትመላለስበት መስሪያ ቤት ያስቀጥሩኛል ብላ ተስፋ የጣለችባቸውና ለዛሬ የቀጠሯትን የመስሪያ ቤቱን ምክትል ስራ አስኪያጅ አዕምሮዋ ውስጥ አስገብታ ነበርና ቦርስዋን ከፍታ፤ ከተጣጠፉት ብሮች መሃከል አንድዋን መዛ አውጥታ ሰጠችው።

ሹፌሩ አሁንም አጭሩ የጅንስ ቀሚስ ወጥሮ ከያዘው ሰውነትዋ ላይ አይኖቹን ሳይነቅል ተቀበላት። ከታክሲዋ ወርዳ መልስዋን ስትቀበል፤ አዕምሮዋ ያለፉትን ጊዚያት ትቶ ላሁኑ ጊዚያት ክፍት ቦታ ስያገኝ፤ ሹፌሩን አወቀችው። 'ጂ ሰ ስ!' አለች በሆድዋ። በሩን 'ጠርቅማበት' እርምጃዋን ቀጠለች።

አሁንም የጎረምሳው ሹፌር አይኖች ከበስተ ኃላዋ መቃኘታቸውን አልተዉም። ከወራት በፊት የመዝገብ ቤት ጸሀፊ የነበረው፤ በአሁኑ ጊዜ ቤተሰቦቹ የገዙለትን 'ውይይት' ታክሲ የሚያሽከረክረው የነቢያት ሺፈራው አይኖች።

አሁንስ ባታያቸውም አስተውላቸዋልች።

ከጌቱ ሀይሉ